# የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና የሙያ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ አስተዳደርና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 770/2013

Health Professionals’ Registration and Licensing Directive No. 770/2021

ጤና ሚኒስቴር
Ministry of Health

መጋቢት 1፥ 2013

## መግቢያ

የጤና ባለሙያዎች የሚሰጡት አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጤና ባለሙያዎችን የምዝገባ፣ የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና የቁጥጥር ስርዓቱን ማጠናከር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጤና ባለሙያዎችን ምዝገባ፣ ሙያ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንደሀገር ወጥ የሆነ አሰራር መከተል አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከደረጃና ደመወዝ ጋር ተያይዞ ቀደም ብሎ ይሰራበት የነበረው የጤና ባለሙዎች ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ በሲቪልሰርቪስ ኮሚሽን የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን መመሪያ በመሻሩ ምክንያት አዲስ ሊያሰራ የሚችል መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፤

በመሆኑ ምበኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 55 (3) እና የምግብ እና መድኃኒት አስተዳደር አወጅቁጥር 1112/2011 አንቀፅ 73 እና ደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀፅ 98 መሰረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## Introduction

Whereas it is important to ensure that the services provided by health professionals are standardized and benefit the community;

Whereas it is important to strengthen the registration, licensing, and regulatory system of health professionals;

Whereas, it is important to establish a nationally uniform system of registration, licensing, and regulation of health professionals;

Whereas it is important to prepare an updated directive based on the replaced Civil Service Commission's job evaluation and grading guideline, and the need to develop a new one,

Now, therefore, this directive under Article 55 (3) proclamation No. 661/2002 of the Ethiopian Food, Drug and Healthcare Administration and Control and the Food and Drug Administration has issued this directive under Article 73 of Proclamation No. 1112/2011 and Article 98 of Regulation No. 299/2006.

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና የሙያ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ አስተዳደርና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር “770/2013” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1. “የጤና ባለሙያ“ ማለት እውቅና ከተሰጠው የትምህርት ተቋም በጤና የትምህርት ዘርፍ የሰለጠነ እና የጤና አገልግሎት ለመስጠት በአስፈጻሚ አካል የተመዘገበ ሰዉ ነዉ፡፡
2. “የጤና ባለሙ ያምዝገባ” ማለት የጤና ባለሙያ ወደ ስራ ከመሰማራቱ በፊት የባለሙያውን መረጃና የሙያ ስያሜ በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ተቆጣጣሪ አካላት የመረጃ ቋት ውስጥ መመዝገብ ማለትነው፤
3. “የሙያ ስራ ፈቃድ” ማለት የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ወይም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማበርከት እንዲችል ለጤና ባለሙያ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤
4. “እክል” ማለት አንድ የጤና ባለሙያ የሙያ ስራውን ሲያከናውን ብቃቱን ወይምሚዛናዊነቱን የሚያዛባ የአዕምሮ ወይምአካላዊ ሁኔታማለትነው፡፡

## Part One
## General Province

### 1. Short title

This directive may be cited as “Health Professionals Registration, Licensing and Regulation Directive No.”770 /2021”.

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise, the following terms shall be interpreted as follows:

1. "Health Professional" means a person trained at a recognized higher educational institution and registered by an executive organ to provide health service.
2. "Health professional registration" means registering a health professional by the Ministry or regional regulatory entities database before engaging in a health service.
3. "Professional Working License" means a certificate issued to health professionals to engage in health care service or to provide other related services.
4. “Impairment” means a physical or mental condition that hindera health professional’s efficiency and balance in a professional service

5. “ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ” ማለት ሚኒስቴሩ ባወጣው መመሪያ መሰረት ማንኛውም የጤና ባለሙያ በስራ ላይ እያለ በሙያው ያገኘውን እውቀትና ክህሎት ጠብቆ እንዲቆይ እና የሙያ ብቃቱን ለማጎልበት በየጊዜው የሚወስደው ሥልጠናና ሌሎች የሙያ ማጎልበቻ ስራዎች ነው፤

6. “እገዳ” ማለት ማንኛውም የጤና ባለሙያ ሚኒስቴሩ ያወጣዉን የቁጥጥር ህግ በመጣሱ ወይም ባለማክበሩ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ሙያዊ ስራውን እንዳያከናውን የማድረግ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤

7. “ስረዛ” ማለት ማንኛውም የጤና ባለሙያ ሚኒስቴሩ ያወጣዉን የቁጥጥር ህግ በመጣሱ ወይም ባለማክበሩ ምክንያት የጤና ባለሙያነት ስራ እስከ መጨረሻው እንዳይሰራ የማድረግ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤

8. “የክልል ተቆጣጣሪ አካል” ማለት በክልል ደረጃ የጤና ባለሙያዎችን የሙያ ስራ ፈቃድ የሚሰጥ አካል ነው፣

9. “ሙያ ስያሜ” ማለት ለባለሙያው በሙያ ፈቃዱ ላይ የሚሰጠው ስያሜ ማለት ነው፣

10. “አጭር ጊዜ” ማለት ከሶስት ወር ያነሰ ጊዜ የሚለውን ያመላክታል፣

11. “የውስን አገልግሎት የምስክር ወረቀት” ከሶስት ወር እስከ አስራ አንድ ወር ጊዜ ከተማሩት ትምህርት ጋር ተያያዥ ለሆነ የክሊኒካል ስልጠና የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

5. "Continuous professional development" means regular training and other professional development activities to ensure that every health professional maintains the knowledge and skills he or she has acquired while in the profession and develops his or her skills.

6. "Suspension" means an administrative measure that prevents any health professional from performing his or her professional duties for a period of time due to violation or non-compliance with the regulations regulated by the Ministry.

7. "Dismissal" means an administrative measure that prevents a health professional from working to the end due to a violation or non-compliance of regulations the Ministry of Health.

8. "Regional regulatory body" means a body that licenses health professionals at the regional level.

9. "Professionaldesignation" means the title given to the professional on the license

10. "Short term" means less than three months.

11. "Limited Service Certificate" means a certificate given to a health professional for clinical training taken over a period of three to eleven months related to the education he/she has received.

12. "በቀጥታ ተዛማጅ የሆነ ስልጠና ወይም ትምህርት" ማለት አንድ ለሁለተኛ ጊዜ የተወሰደ የተለየ ስልጠና (specific training) የመጀመሪያውን የተለየ ስልጠና (specific training) እንደ ቅድመ ሁኔታ በአስገዳጅ ሁኔታ የሚወስድ ከሆነ ወይም በተማሳሳይ ዘርፍ ትምህርቱን ያሻሻለ ከሆነ ማለት ነው፡፡

13. "ሮቴቲንግ ኢንተርን " ማለት የመጨረሻ አመት የጠቅላላ ህክምና፣ የጥርስ ህክምና ወይም ፊዚዮቴራፒ ህክምና ልምምድ ላይ ያለ ተማሪ ማለት ነው፡፡

14. "ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ (Authenticated)" ማለት ውጭ ሀገር የተማረ ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ መስራት የሚፈልግ የውጭ ሀገር ዜጋ የትምህርት ወይም ተያያዥ ማስረጃዎች ትክክኛ ስለመሆናቸው የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፊርማ እና ማህተም በማስቀመጥ ያረጋገጠው ማለት ነው፡፡

15. "የውል ግዴታ ያለባቸው" ማለት የጤና ባለሙያው ትምርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ስፖንሰር አድርጎ ያስተማረውን ተቋም ለሚታወቅ የጊዜ ገደብ (ለተወሰነ ጊዜ) ተመልሶ ለማገልገል ወይም የታወቀ የገንዘብ መጠን ሊከፍል ተስማምቶ ውል የገባ ማለት ነው፡፡

16. "ጊዜያዊ የሙያ ፈቃድ" ማለት የትምርት ውል ግዴታ ላለባቸው የጤና ባለሙያዎች ግዴታቸውን እስኪጨርሱ ድረስ የውል ግዴታ ለገቡበት ተቋም የሚሰጥ የሙያ ስራ ፈቃድ ማለት ነው፣

17. "ሚኒስቴር" ማለት ጤና ሚኒስቴር ማለት ነው፡፡

12. "Directly related training or education" means the second specific training received for the second time is either dependant on or take a first specific training as a prerequisite, or if you improve your education in a similar field of study.

13. "Rotating Intern" means a final year student who is practicing general medicine, dental medicine, or physiotherapy.

14. "Authenticated" means an Ethiopian-educated abroad or a foreigner wishing to work in Ethiopia certifying the authenticity of educational or related documents by signing and stamping the Ethiopian Ministry of Foreign Affairs.

15. "A professional with contractual obligation"means after completing the course, the professional agrees to return to the sponsoring institution for a specified period of time (for a limited time) or to pay a fixed amount.

16. "Temporary Professional License" means issuing a professional working license by a regulatory organ to sponsoring institution of a health professional who has a contract until the end of the term.

17. "Ministry" means the ministry of health

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገር ውስጥ የጤና አገልግሎት ለመስጠት የሙያ ስራ ፈቃድ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ውጭ ሀገር ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ለተማሩ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የጤና ባለሙያዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ፡-

1. ህብረተሰቡ ሙያዊና ስነምነግባራዊ ብቃት ባላቸው የጤና ባለሙያዎች የጤና አገልግሎት እንዲያገኝ ማስቻል፤
2. የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና የሙያ ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ በግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓት እንዲፈጸም ማስቻል፤

## 3. Scope of Application

This Directive shall apply to Ethiopian or non-Ethiopian health professionals who have applied for a professional license to provide health services in the country.

## 4. Objective

Purpose of this Directive is:

1. To enablethe community have access to health services by professionally and ethically qualified health professionals.

2. To ensure transparency and accountability in the registration and licensing system of health professionals

ክፍል ሁለት

## የጤና ሙያን ለመሰየም እና የሙያ ስራ ፈቃድ ለመስጠት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች

### 5. የጤና ሙያ ስልጠናውን በሀገር ውስጥ ላጠናቀቀ ኢትዮጵያዊ የጤና ባለሙያ የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች

ማንኛውም በሀገር ውስጥ ሰልጥኖ የመጣ የጤና ባለሙያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ካሟላ የሙያ ስራ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፤

1. በትክክል የተሞላ የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ ፎርም፤
2. ከተመረቀበት ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ የተሰጠ የተማረውን የሙያ ዓይነትና ትምህርቱን ስለማጠናቀቁ የሚገልፅ ማስረጃ (ሰርተፊኬት፣ ዲፕሎማ፣ ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ፣ ዲግሪ እና ትራንስክሪፕት) እና መጨረሳቸውን የሚያረጋግጥ ዝርዝር ከተማሩበት የትምህርት ተቋም ለሚኒስቴሩ ወይም ለክልል ተቆጣጣሪ አካላት መምጣት አለበት፤
3. የሙያ ብቃት ምዘና ፈተና እየተሰጠባቸው ላሉ የሙያ ዘርፎች የሙያ ብቃት ምዘና ፈተና ያለፈ መሆኑን በመዛኙ አካል የተረጋገጠ ማስረጃ
4. ስድስት ወር ያላለፈው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ፤

## PART TWO

## REQUIREMENTS FOR HEALTH PROFESSIONAL REGISTRATION AND LICENSING

### 5. Requirements for an Ethiopian Health Professional who has completed his / her training in the country

Any locally trained health professional can be issued a professional license if he/she meets the following requirements :

1. Properly completed Professional Registration and Licensing Request Form
2. Should present authenticated academic credentials from the training institution mentioning his/her completion and the type of profession graduated (Certificate, Diploma, Degree or Diploma, Degree and Transcript) from the college or university in which he/she graduated) to the ministry or regional regulatory bodies.
3. For competency assessment-based professions, a piece of evidence verified by the assessing entity indicates that the examinee has passed the competency assessment examination.
4. Two passport-sized photos taken not more than six months.

5. የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበት ደረሰኝ፤
6. ሦስት ወር ያላለፈው የጤና ምርመራ ሰርተፊኬት፣
7. በሙያቸው ለተወሰነ ጊዜ ለማገልገል የውል ግዴታ ላለባቸው ባለሙያዎች ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ባለሙያው የውል ግዴታውን በአገልግሎት ወይም በገንዘብ መጨረሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከአንድ እስከ ስድስት ያሉትን የሚያሟላና ንዑስ አንቀጽ ሰባት የተሚመለከተውን መስፈርት ባያሟላ የውል ግዴታ እንዳለበት የሚገልጽ ጊዜያዊ የሙያ ፈቃድ ውል ላስገባው ተቋም ይሰጠዋል፡፡

## 6. በውጭ ሀገር የሰለጠኑ የጤና ባለሙያ የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘት ማሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች

ማንኛውም በውጭ ሀገር ሰልጥኖ የመጣ የጤና ባለሙያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ካሟላ የሙያ ስራ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፤

1. በትክክል የተሞላ የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ ፎርም፤
2. ከተመረቀበት ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ የተሰጠ የተማረውን የትምህርት ዓይነትና ትምህርቱን ስለማጠናቀቁ የሚገልፅ ህጋዊነቱ የተረጋገጠ (Authenticated) የትምህርት ማስረጃ (ሰርተፊኬት፣ ዲፕሎማ፣ ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ፣ ዲግሪ እና ትራንስክሪፕት)

5. Service fee receipt
6. A medical examination certificate that does not exceed 3 months
7. For agreement committed professionals, a piece of evidence which confirms that the professional has completed his/her contractual obligation with service or money.
8. If a professional meets the requirement of sub-clause 1 – 6 of this article and does not meet 7 under the current article, a temporary professional license shall be given to the contracting entity/organization.

## 6. Requirements for licensing health professional who trained abroad

Any foreign-trained health professional may obtain a professional license if he/she fulfils the following requirements:

1. Properly completed Professional registration and licensing application Form.
2. Should present authenticated academic credentials (Certificate, Diploma, Degree or Diploma, Degree and Transcript) from the college or university in which he/she graduated.

3. ከከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ (HERQA) የተሰጠ የአቻ ግመታ (Equivalence) ማቅረብ፤
4. ስድስት ወር ያላለፈው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ፤
5. የፓስፖርት ኮፒ
6. የጤና ምርመራ ሰርተፊኬት
7. ለአገልግሎት የተከፈለበት ደረሰኝ

## 7. በውጭ ሀገር የሰለጠነ ኢትዮጵያዊ የጤና ባለሙያ የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች

ማንኛውም በውጭ ሀገር ሰልጥኖ የመጣ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የጤና ባለሙያ፣ የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘት በአንቀፅ "6" ከተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች በተጨማሪ፤

1. በሙያው ለተወሰነ ጊዜ ለማገልገል የውልግ ዴታ ላለበት ባለሙያ የውል ግዴታ ካስገባው ተቋም የሙያ ስራ ፈቃድ እንዲያወጣ የሚፈቅድ የስምምነት ደብዳቤ፣ ወይም ባለሙያው የውል ግዴታውን በአገልግሎት ወይም በገንዘብ መጨረሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤
2. ስራ ላይ የነበረ ከሆነ ወቅታዊ የሆነ በሙያው መመዝገቡን የሚያረጋግጥ ህጋዊነቱ የተረጋገጠ (Authenticated) የሙያስራፈቃድ፣

3. Equivalence letter from Higher Education Relevance and Quality Agency (HERQA)
4. Two passport size photograph not exceeding six months
5. Copy of a Passport
6. Medical examination certificate
7. Service fee receipt

## 7.Requirements for an Ethiopian health Professional Trained abroad to get professional license

Any Ethiopian or an Ethiopian-born foreigner needs to fulfill the following requirements in addition to the listed under Article “6” above.

1. For agreement committed professionals, a piece of evidence which confirms that the professional has completed his/her contractual obligation with service or money.
2. If he/she was practicing, shall present authenticated evidence indicating that he/she is a registered and has professionallicens.

3. ስራ ላይ የነበረ ከሆነ በሙያው ስራ ላይ ስለመሆኑ የሚገልፅ ማስረጃ
4. ባለሙያዎቹ የመጡበት ሀገር የሙያ ስራ ፍቃድ አሰጣጥ ስርአት ከእኛ ሀገር ጋር የማይመሳሰል ከሆነ የሚጠይቁት የሙያ ስራ ፈቃድ የትምህርት እና የስራ ልምድ መረጃቸውን መሰረት አድርጎና ከመጡበት ሀገር የሙያ ፈቃድ ሠጪ አካል በሚላክ የማብራራሪያ ደብዳቤ (verification) መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡

3. If he/she was practicing, a shred of evidence indicating that he/she is practicing the profession (work experience).
4. If the professional licensing system from a country of origin is not the same as Ethiopia, they shall be served based on their educational document, experience and an additional verification letter from the country from which they came from.

## 8. በውጭሀገር በጤና ሙያ የሰለጠነ የውጭሀገር ዜጋ የጤና ሙያ ስራፈቃድለማግኘት መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች

ማንኛውም በውጭ ሀገር ሰልጥኖ የመጣ የውጭ ሀገር ዜጋ የጤና ባለሙያ የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘት በአንቀፅ "6" ከተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች በተጨማሪ፤

1. የሙያ ስራፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅለት የሀገር ውስጥ ተቋም፤
2. በአንቀጽ (6) ንዑስአንቀጽ (2) እና (3) ቢኖርም የጤና ባለሙያዎችን ለአጭር ጊዜ አገልግሎት የሚያስመጣ የሀገር ውስጥ ተቋም የባለሙያዎቹ የትምህርት ማስረጃና የሙያ ስራ ፈቃድ ህጋዊነት ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ (Authenticated) ካልሆነ የማስረጃዎቹን ትክክለኛነትና ከዚህ ጋር ተያይዘው ለሚቀርቡ ማንኛውም ጥያቄዎችና ችግሮች ኃላፊነት እንደሚወስድ ለሚኒስቴሩ በደብዳቤ በማሳወቅ ፈቃድ መጠየቅ ይችላል፣
3. ባለሙያዎቹ የመጡበት ሀገር የሙያ ስራ ፍቃድ አሰጣጥ ስርአት ከእኛ ሀገር ጋር የማይመሳሰል ከሆነ የሚጠይቁት የሙያ ስራ ፈቃድ የትምህርት እና የስራ ልምድ ማስረጃቸውን መሰረት አድርጎና ከመጡበት ሀገር የሙያ ፈቃድ ሠጪ አካል በሚላክ ማብራሪያ ደብዳቤ (verification) መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል፣

## 8. Requirements of Foreign Health Professionals who trained abroad and seek to get a professional license

In addition to the conditions set out in article "6," any foreign health professional should have fulfilled the following prerequisite to obtain a professional working license.

1. Local institution that requests a professional license to be given for the foreign professional
2. In accordance with sub-article (2) and (3) of the article (6)a local institution that requests short-term services license to health professionals, if the legality of the professional education, professional license, and the relevant documents is not verified by the authorized body, he/she can request a license by writing to the Ministry mentioning he will take any questions or concerns regarding the legality
3. If the professionals are from a country where the professional licensing system is not the same as ours, they will ask for a license based on their education, work experience, and a letter of verification from the professional's home country.

4. እንግሊዝኛ ተናጋሪ ካልሆኑ እና ስርዓተ ትምህርቱ በእንግሊዝኛ ከማይሰጥባቸው አገሮች ለሚመጡ የውጭ ሀገር ዜጎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማቅረብ እንዲሁም የሚያቀርቡት የትምህርት ማስረጃ የሙያ ፈቃድ እና አሰፈላጊ መረጃዎች ሁሉ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ካልሆነ ህጋዊ በሆነ አካል ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመ መሆንይ ኖርበታል፡፡
5. ለባለሙያዎች ፈቃድ ጠይቆ የሚያሠራ ተቋም ባለሙያውን ለማሰራት የሚያስችል የታደሰ የተቋሙን ፈቃድ ማቅረብ ይኖርበታል
6. በሙያው ስራ ላይ ስለመሆኑ የሚገልፅ ማስረጃ
7. ባለሙያው በኢትዮጵያ ቆይታው የሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ቢፈፅምና ሳይጠየቅ ወደ ሀገሩ ቢመለስ ያስመጣው አካል ኃላፊነቱን ይወስዳል
8. በዚህ አንቀፅ ተራ ቁጥር "7" የተገለፀው እንደተጠ በቀሆኖ አስመጪው አካል የሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት የፈፀመውን ባለሙያ ተጠያቂ ለማድረግ ከመጣበት ሀገር ከሚገኝ ተቆጣጣሪ አካል ወይም አቻ ተቋም ጋር በሚደረገው የመረጃ ልውውጥ ሚኒስቴሩ አጋዥ ደብዳቤ ሊፅፍ ይችላል
9. በዚህ አንቀ ፅተራ ቁጥር "4" የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባሙያዎቹ ለአጭር ጊዜ የሚመጡ እና የእንግሊዝኛ ችሎታ ሰርተፊኬት ማቅረብ ያልቻሉ ከሆነ በሚያስመጣው ተቋም ኃላፊነት የስራ ሙያ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል፤ ለማስረዘም ከፈለጉ ግን የእንግሊዘኛ ችሎታ ሰርተፊኬት ማቅረብ አለባቸው፡፡

4. If the foreign professional came from a non-English speaking country and the curriculum is non-English, he/she must provide an English language proficiency certificate and if all educational credentials and other related documents are written in non English language, it shall be translated into English by a legal entity.
5. The hiring institution that requests a license for a foreign profession must provide a renewed institutional license that enables it to hire the professional.
6. Evidence that he is practicing his/her profession (work experience)
7. If the professional commits professional misconduct during his stay in Ethiopia and returns to the country unsolicited, the hiring institution shall be liable.
8. Notwithstanding the provisions of Article 7 of this Article, if the importer communicates with the professional home country regulatory body or equivalent institution to make the professional who commits misconduct accountable, the Minister may write a support letter during the exchange of information.
9. Subject to the provisions of this article sub-article 4, if foreign health professionals came to Ethiopia for a short period and cannot provide a certificate of English proficiency, they may be licensed by the responsibility of the importing institution. But if the institution wants to extend it, he/she must have an English proficiency certificate.

## 9. የዉስን አገልግሎት የምስክር ወረቀት

1. ይህ የሙያ ስራ ፈቃድ ባለሙያው ከያዘው የትምህርት ደረጃ የስራ ወሰን በላይ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ከሦስት እስከ አስራ አንድ ወር ጊዜ የሚወሰድ ስልጠና ለወሰደ የጤና ባለሙያ የሚፈቀድ ይሆናል
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሙያዎቹ የሙያ ስራ ፈቃድ ማቅረብ ሳያስፈልጋቸው አሰሪ መስሪያ ቤቱ ሊያሰራቸው ይችላል
3. በዚህአንቀፅንኡስአንቀፅ (1) እና (2) እንደተጠበቀሆኖየማስረጃዎቹንትክክለኛነትናከዚህጋርተያይዘውለሚቀርቡ ማንኛውምጥያቄዎችናችግሮችአሰሪ መስሪያቤቱኃላፊነትእንደሚወስድለ ሚኒስትሩወይምለክልልተቆጣጣሪአካ ላትበደብዳቤማሳወቅአለበት፡፡

## 9. Certificate of Limited Service

1. This professional license shall be permitted for a health professional that has undergone three to eleven months training to perform tasks beyond the level his/her educational level.
2. Subject to sub-article (1) of this article, the hiring institution may assign the professionals to practice without the need to provide a professional license.
3. Subject to sub-articles (1) and (2) of this Article, the employing institution shall inform to the Ministry or the regional regulatory body that it is responsible for the accuracy of the evidence and any related issues.

10. የሙያ ስያሜ አሰጣጥ

1. ለባለሙያ የሚሰጥ የሙያ ስያሜ የባለሙያውን የትምህርት ዝግጅት መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡
2. በተራቁጥር 1 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ ለባለሙያው የሚሰጠው የሙያ ስያሜ አገልግሎትን መሰረት በማድረግ Junior, Senior, Chief, Expert, Senior Expert, Chief Expert እና Consultant በሚል ይሆናል
3. የሙያ ስያሜ ከአንዱ ስያሜ ወደ ቀጣይ ስያሜ ለመሸጋገር 3 ዓመት በሙያው መስራት ይኖርበታል
4. የሙያ ስያሜዎቹ በትምርት ደረጃ (ዲፕሎማ፣ ዲግሪ፣ ማስተርስ፣ ወዘተ…) እራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ይሆናል (ከአንደኛው ደረጃ ወደ ሌላኛው ደረጃ የሚሻገር የስራ ልምድ አይኖርም)
5. ይህ የሙያ ስያሜ አሰጣጥ ከደመወዝ እና ከደረጃ እድገት ጋር ግንኙት የለውም
6. ማስተርስ፣ህክምናና ከዚያ በላይ ያሉ ባለሙያዎች ኮንሰልታንት ደረጃ ለመድረስ 15 ዓመት የስራ ልምድ እና ሁለት ጥናት በታወቀ ጆርናል ማሳተም የሚጠበቅባቸው ሲሆን አተገባበሩም፡-
   ሀ. በግሉ ወይም የምርምሩ ባለቤት (principal investigator) ሆኖ ምርምር ከሰራ
   ለ.ምርምሩን በታወቀ ጆርናል ማሳተሙን በጤና ሚኒስቴር በሰው ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት ተረጋግጦ ማስረጃ ሲቀርብ

ከላይ "ሀ" እና "ለ" የተጠቀሱትን ካሟላ ሁለት ጥናት እንደ አንድ ዓመት የስራ ልምድ ይያዝለታል ሆኖም በሦስት አመት ውስጥ ከሁለት በላይ ምርምር ቢያሳትም ተጨማሪ እንደ ስራ ልምድ አይያዝለትም

**10. About Professional nomenclature**

1. Professional nomenclature shall be based on the educational level of the professional.
2. As mentioned in Figure 1, the professional designation will be labeled as Junior, Senior, Chief, Expert, Senior Expert, Chief Expert, and Consultant based on the level of professional experience
3. A Professional must serve for 3 years in the profession to transfer from one professional designation to the next.
4. Professional designations in education Level (Diploma, Degree, Masters, etc.) are self-sufficient and no work experience will be transferred from one educational level to another.
5. This professional designation has nothing to do with salary increment and promotion.
6. For a master's, Medicine, and above professionals, a minimum of 15 years of work experience and publication of two research work in a well-known journal is required. The implementation will be:

A. If he/she are conducts the research on private or as a principal investigator,
B. If you submit a piece of confirmed evidence from the Ministry, human resource development directorate regarding the publication of the work in a well-known journal.

If he/she presents the above two publications, he will be considered as having one year of work experience, but if he/she has more than two publication with-in three years it will not be considered as an additional work experience.

7. የሙያ ፈቀድ የሚሰጠው መመዝገብ ግዴታ ለሆነባቸው የሙያ ዘርፎች ነው፡፡
8. የብቃት ምዘና ፈተና መውሰድ የሚገባቸው የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ የሚያገኙት ፈተናውን ሲያልፉ እና በፈታኙ አካል ሲረጋገጥ ይሆናል
9. በሰብ-ስፔሻሊቲ ወይም በሱፐር-ርስፔሻሊቲ ከአንድ አመት በታች ተምሮ የመጣ ባለሙያ ካጋጠመ ሙያው የሰብ-ስፔሻሊቲ ወይም ሱፐር-ስፔሻሊቲ ደረጃ መሆኑን በሰው ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት ማረጋገጫ ሲቀርብ የሙያ ስራ ፍቃድ ይሰጠዋል
10. ሚኒስቴሩ ለሙያ ስያሜ አሰጣጥ አስቸጋሪ የሆነ ሙያ ሲያጋጥም በሚኒስቴሩ የሰው ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ይስተናገዳል
11. የሙያ ስያሜ አሰጣጥን በተመለከተ በእዝል ሦስት ላይ ያለውን ማየት ይቻላል

7. Professional working license shall be given to those professions with an obligation to be registered
8. Health professional who should take competency assessment examinations shall obtain their license after passing the examination and verified by the examining entity.
9. If there is a professional who comes with a sub or super-specialty level with less than one year of training verification shall be provided from human resource development directorate that the profession is in the level of sub/super specialty and the license shall be given afterward.
10. The Ministry shall, in the event of unforeseen circumstances, be dealt with following the decision of the human resource development directorate of the Ministry.
11. See Appendix 03 about professional designation procedures.

**11. ስለ ሞያ ስራፈቃድአሰጣጥ**

1. ማንኛውም የሙያ ስራ ፍቃድ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ለሙያ ስራ ፈቃድ በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ተቆጣጣሪ አካላት የተቀመጡትን መስፈርቶችን ካሟላ የሙያ ስራ ፈቃድ ያገኛል፡፡
2. ማንኛውም ሰው የሚያቀርበው የትምህርት ማስረጃ እውቅና ካለው የትምህርት ተቋም መሆን አለበት
3. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የክሊኒካል ተግባር ልምምድ በሚፈልጉ የሙያ መስኮች በማታ፣ በርቀት፣ በኦንላይን፣ በእረፍት ቀናት ትምህርት መሰጠት ስልጣን ባለው አካል ከተከለከለበት ጊዜ በኋላ ተምሮ ቢመጣ የሙያ ፈቃድ አይሰጠውም
4. ሚኒስቴሩ ወይም የክልል ተቆጣጣሪ አካል በጤና ሙያ መስክ ለመሰማራት ጥያቄ የሚያቀርብ የጤና ባለሙያን ማስረጃ በመመርመር ይመዘግባል፣ የሙያስያሜይሰጣል፣ የሙያ ስራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
5. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከአንድ በላይ በሆኑ የጤና ሙያ መስኮች ለመሰማራት የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘ ትጥያቄ ሲያቀርብ ጥያቄውን መሰረት ያደረገ ሁሉንም ሙያዎች ያካተተ የሙያ ስራ ፈቃድ በአንድ ላይ ማግኘት ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አምስት(5) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከመጀመሪያ ሙያው በቀጥታ ተዛማጅ የሆነ ስልጠና ከወሰደ መጨረሻ ባገኘው ወይም በፍላጎቱ በመረጠው ሙያ በአንዱ ብቻ ሊመዘገብና የሙያ ስራ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

**11. Regarding professional license provision**

1. Any person applying for a professional license at the Ministry or regional regulatory and meet all the requirements shall receive a professional license.
2. All educational evidence presented must be from a recognized educational institution.
3. No health professional shall be granted a professional license when he or she is educated in a professional field requiring clinical practice and, on an extension, distance, online, and weekends basis after it's prohibited by the authorized body.
4. The Ministry or regional regulatory bodies shall examine the educational evidence presented, register and provide professional license who applies to practice with his/her profession.
5. When any health professional can applies for a professional licensein more than one profession and professional license shall be given by including all the professions, on a single license.
6. Notwithstanding the provisions of sub-article (5) of this article, any health professional who has received training that is directly related to his or her profession may be enrolled in only one of the professions he or she has acquired lastly or of his / her choice.

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አምስት (5) እና ስድስት(6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ባለሙያው ፈቃድ ለማግኘት ጥያቄ ባቀረበባቸው ሙያዎች ሁሉ ለሙያ ምዝገባና ፈቃድ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

8. ሚኒስቴሩ ወይም የክልል ተቆጣጣሪ አካላት ባለሙያው ለእያንዳንዱ ሙያ ያቀረባቸውን ማስረጃዎች ህጋዊና ትክክለኛ ካልሆኑ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ፈቃዱን መከልከል ይኖርበታል፡፡

9. የሶስት አመት የሙያ ስራ ፈቃድ ለባለሙያው የሚሰጥ ሲሆን ጊዜያዊ ፈቃድ እና የአጭር ጊዜ ፈቃድ ለጠያቂ ተቋም የሚሰጥ ይሆናል፡፡

10. ሀገር ውስጥ ለመስራት ፈቃድ የተሰጣቸው የውጭ ሀገር ዜጎች በልዩ ስምምነት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የሶስት አመት ፈቃድም ለተቋም የሚሰጥ ይሆናል፡፡

11. የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውን፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ለመሆናቸው መረጃ አቅርበው እንደ ኢትዮጵያዊ ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

7. In accordance with the provisions of Articles 5 and 6, a health professional must meet the requirements for professional registration and licensing in all professions in which he/she is applying for a license.

8. The Ministry or regional regulatory bodies shall reject the application if the evidence provided by the professional is not legal and/or invalid.

9. Three years professional working license shall be given for the professional, temporary license and a short-term license shall be given to the requesting institution only.

10. Except for a special agreement for foreign nationality health professionals who have been granted a professional in the country, a three-year permit will also be issued to the institution.

11. Foreign nationalities of Ethiopian descent may be treated as Ethiopians by providing evidence that they are of Ethiopian descent.

12. ከሙያ ስራ ወሰን ውጭስለመስራት

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከተመዘገበበት የሙያ ስራ ወሰን ውጪ የጤና አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡ ሆኖም በልዩ አስገዳጅ ሁኔታ ከሚኒስቴሩ ሲጠየቅና ፈቃድ ሲያገኝ ከተመዘገበበት ሙያ ውጪ ጊዜያዊ የሙያ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከስራ ወሰኑ ውጪ በልዩ አስገዳጅ ሁኔታ ለሚሰጠው ተጨማሪ የጤና አገልግሎት ስልጠና መውሰድ ይኖርበታል፡፡
3. በልዩ አስገዳጅ ሁኔታ በጤና ባለሙያው እንዲከናወኑ የሚሰጡ ተጨማሪ የጤና አገልግሎቶች በፅሁፍ የተደገፉ ሆነው በባለሙያው ቢከናወኑ በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትሉና በባለሙያው በብቃት ይከናወናሉ ተብለው የታመነባቸው ብቻ መሆን አለባቸው፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንተጠበቀ ሆኖ ከተመዘገቡበት የሙያ ፈቃድ ተዋረድ በታች የሆነ ፈቃድ የሚጠይቅ አገልግሎት ለመስጠት ጊዜያዊ የሙያ ስራፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤ ለሚሰጠውም አገልግሎት ለባለሙያዎቹ ፈቃድ የሚጠይቅና ሀላፊነቱን እንደሚወስድ በደብዳቤ የሚገልጽ አካል ወይም ተቋም ሊኖር ይገባል፡፡

**12. Working outside the Occupational Term**

1. No health professional can provide health services if not registered. Provided, however, that the service may be provided temporarily outside of the profession in which it is registered, upon request and approval by the Ministry during some extraordinary circumstances.
2. Subject to sub-article (1) of this article, any health professional shall undergo additional training for the special health care provided under the contract.
3. Additional health services provided by a health care professional in a special compulsory manner shall be supported by a written document from the institution and shall be considered practiced by the professional competently and will not be harmful to the community.
4. Subject to sub-article (1) of this Article, a temporary professional license may be granted for a service that requires a license below the registered professional hierarchy and there shall be an organ/insitute that request with an official letter and will take the accountability.

13. የሙያ ስራፈቃድስለማደስ

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሰጠውን የሙያ ስራ ፈቃድ በሦስት አመት ማሳደስ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሰጠውን የሙያ ስራ ፈቃድ የጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ አንድ ወር በፊት የእድሳት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ለሙያ ፈቃድ እድሳት የሚያመለክት ባለሙያ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

ሀ. በትክክል የተሞላ የማመልከቻ ቅጽ፤

ለ. ከዚህ በፊት የተሰጠ የሙያ ስራ ፈቃድ መመለስ፤

ሐ. ስራ ላይ መሆኑን የሚገልጽ የስራ ልምድ ከአሰሪው ተቋም ማቅረብ፣

መ. በ "ሐ" የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከግል ወይም መንግስታዊ ካልሆነ ተቋም የሚቀርብ የስራ ልምድ የገቢ ግብር ስለመክፈሉ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት

ሠ. በተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ መመሪያ ላይ የተቀመጠውን የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ መውሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ (ግዴታ ላለባቸው የሙያ ዘርፎች የሙያ ማጎልበቻው መሰጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ)

ሰ. ስድስት ወር ያላለፈው ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍ፤

ረ. የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ

ሠ. የጤና ምርመራ ሰርተፊኬት

4. ከአንድ ሙያ በላይ ለመስራት የሙያ ስራ ፈቃድ ያገኘ ባለሙያ ለእያንዳንዱ ሙያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

**13. Renewal of professional license**

1. Every health professional should renew the professional license evry three years
2. Every health professional must apply for a professional license renewal one month before the expiration of that professional license.
3. The one who requests professional license renewal must meet the requirements

A. Correctly filled application form

B. Return of professional license given previously

C. Current work experience from the employer institute

D. Notwithstanding"C" the work experience issued by the private or nongovernmental institute should present income tax settlement confirmation.

E. An evidence confirming that they have taken continuous professional development course as indicated by the directive (to those professionals who shall take the CPD course starting from the date of delivery of CPD)

F. Two passport size photographs not more than 6 months

G. Service fee receipt

H. Health examination certificate

4. A professional who fulfilled the requirement and got more than one professional license shall meet the requirements set out in sub-article (3) of this Article for each request to renew.

5. ትምህርቱን በውጭ ሀገር ያጠናቀቀ ኢትዮጵያዊ፤ በሚኒስቴሩ የሙያ ስራ ፈቃድ የተሰጠውና በሀገር ውስጥ የሚሰራ የጤና ባለሙያ የሙያ ስራፈቃዱን የሚያሳድሰው በሚሰራበት ክልል በሚገኝ የክልል ጤና ተቆጣጣሪ አካል ይሆናል
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ስር በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሙያ ስራ ፈቃዱን ያላሳደሰ ባለሙያ ከሦስተኛው ዓመት መጨረሻ ቀን ቀጥሎ ባለው ቀን ጀምሮ ከእድሳት የአገልግሎት ክፍያው በተጨማሪ በየወሩ ለእድሳት የተቀመጠውን የክፍያ መጠን ሶስት እጥፍ ቅጣት በመክፈል ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት ማሳደስ ይችላል (በሀገራዊ ግዳጅ ላይ፣ በጤና ችግር ላይ ወይም በማረሚያ ቤት እያለ የእድሳት ጊዜው ያለፈውን ባለሙያ አይመለከትም)
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ(1)፣ (2) ፡(5) እና (6) መሠረት ሳያሳድስ የቀረ ባለሙያ ያለሙያ ስራ ፈቃድ እንደሰራ ተቆጥሮ በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ተቆጣጣሪ አካላት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

5. A person who has completed his/her education abroad and gets licensed by the Ministry and working in Ethiopia, shall renew his/her license with the regional regulatory bodies where he/she works.
6. If the professional does not renew his/her professional license during the period based on Sub-articles (1) and (2) of this article, starting from the next day of the deadline, in addition to the service fee, he/she shall pay three folds of the renewal fee in each month and can renew his professional license in the next six months (This excludes those who are in national duty, in health problem or imprisonment).
7. A professional who fails to renew following sub-article (1) (2) (5) and (6) of this Article shall be deemed to have acted without a professional license and shall be subject to disciplinary action by the Ministry or the Regional regulatory bodies.

## 14. የተሰጠየሞያ ስራፈቃድየሚሰራበትጊዜ

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በተሰጠው የሙያ ስራ ፈቃድ ሳይሰራበት ከቆየ በሰንጠረዥ 1 መሰረት በበሳል ባለሙያ ክትትል ስር ልምምድ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ለተቆጣጣሪው አካል ሳያሳውቅ በሙያው ሲሰራ ቢገኝ ባለሙያው ያለ ሙያ ስራ ፈቃድ ሲሰራ እንደተገኘ ተቆጥሮ በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ተቆጣጣሪ አካላት አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶበት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) መሰረት እንዲሰራ ይደረጋል፡፡
3. በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ተቆጣጣሪ አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ከሙያው ተለይቶ ለቆየ ባለሙያ የሙያ ዘርፉ አገር አቀፍ የብቃት ምዘና የሚሰጥበት ከሆነ ለሶስት ወር በበሳል ባለሙያ ክትትል ስር እንዲሰራ ተደርጎ ምዘናውን በሚሰጠው አካል ብቃቱ በፈተና ተመዝኖ ማለፍ ሲችል ወይም የሙያ ዘርፉ አገር አቀፍ የብቃት ምዘና የሚሰጥበት ካልሆነ በሰንጠረዥ 1 መሰረት በበሳል ባለሙያ ክትትል ስር እንዲሰራ ተደርጎ ሲያጠናቅቅ እና ለልምምድ ከተመደበበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ ማግኘት ሲችል እና የሙያ ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልገውን ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ሲችል በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ተቆጣጣሪ አካላት ፍቃድ ይሰጠዋል፡፡
4. በሰለጠነበት የሙያ ዘርፍ በተከታታይ ከአስር አመት በላይ ያልሰራ ባለሙያ ተመልሶ ወደዘርፉ መግባት አይችልም፡፡

## 14. Period of professional license is not functional

1. If any health professional has not performed using the given professional license, he or she will practice under the supervision of experienced professional in accordance with Table 1.
2. If it is found to be operating without informing the regulatory body following sub-article (1) of this Article, it shall be deemed to have been obtained without a professional license and administrative action shall be taken by the Ministry or regional regulatory bodies and will subject to practice under supervision in accordance with sub-article (3) of this Article.
3. Based on this article sub-article /3/ those professionals who were off duty, if their profession is included on the national licensure examination and pass the licensure exam after three months of under supervision practice or if the profession is not included in national licensure examination he/she will continue or be assigned under supervision in accordance with table 1 and can get a professional license after completion of his/her under supervision and bring a piece of evidence from the institution.
4. A professional who has not engaged in the professional practice for more than 10 consecutive years shall not be continue as a profession

ሰንጠረዥ 1፡ አንድ ባለሙያ ልምድ ባለው ጤና ባለሙያ ስር በክትትል የሚቆበትን ጊዜ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ/ቁ | በስራላይየቆየበትጊዜ | ባለሙያው ከስራ ውተለይቶ የቆየበት ጊዜ | በበሳል ባለሙያ ስር በክትትል የሚቆበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | ምንምያልሰራ | ከሁለት እስከ ሦስት ዓመት | ለስድስት ወር |
| 2 | ምንምያልሰራ | ከሦስት እስከ አምስት ዓመት | ለአንድ ዓመት |
| 3 | እስከ 5 ዓመት | ከሁለት እስከ ሦስት ዓመት | ለስድስት ወር |
| 4 | ከ5 እስከ 10ዓመት | ከሦስት እስከ አራት ዓመት | ለስድስት ወር |
| 5 | ከ 10 እስከ 20 ዓመት | ከአራት እስከ አምስት ዓመት | ለስድስት ወር |
| 6 | ከ 20 ዓትበላይ | ከአምስት እሰከ አስር ዓመት | ለአንድ ዓመት |
| 7 | ከ 20 ዓትበላይ | ከአስር ዓመት በላይ | በጤና ሙያ መሰማራት የለበትም |

Table 1: a table which indicates the period where a professional stays under the follow up of experienced health professional

| No. | On Duty | Off Duty | Period under follow up with experienced professional |
|---|---|---|---|
| 1 | Not working | From two up to three years | For six months |
| 2 | Not working | From three up to five years | For One year |
| 3 | Up to five years | From two up to three years | For six months |
| 4 | From five to – 10 years | From three up to four years | For six months |
| 5 | From 10 – 20 years | From four to five years | For six months |
| 6 | Over 20 years | From five upto ten years | For one years |
| 7 | Over 20 years | Over ten years | Should not work as health professional |

**15. በውጭ ሀገር የሰለጡ የጤና ባለሞያዎችን በኢንተርንሽፕ ወይም ኤክስተርንሽፕ ልምምድ ስለመመደብ**

1. ከመሰረታዊ የጤና ሙያ ስልጠናው ጀምሮ በውጪ ሀገር ስልጠና ወስዶ ለሙያ ምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው በሰለጠነበት ሀገር በሙያው የተመዘገበ መሆኑንና አገልግሎት መስጠት መቻሉን የሚገልፅ ፈቃድ ካቀረበ ኢንተርንሺፕ እንዲሰራ አይገደድም፡፡
2. ከመሰረታዊ የጤና ሙያ ስልጠናው ጀምሮ በውጪ ሀገር ስልጠና ወስዶ ለሙያ ምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው በሰለጠነበት ሀገር በሙያው እንዲሰራ ያልተመዘገበና ፈቃድ ከሌለው ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ ኢንተርንሺፕ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ተራቁጥር (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ሙያው የብቃት ምዘና ፈተና የሚሰጥበት ከሆነ የብቃት መመዘኛ ፈተና ወስዶ ሲያልፍ እና ሌሎች መስፈርቶችን ሲያሟላ ሙያ ፈቃድ ማግኘት ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ተራ ቁጥር(1) እና (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሙያው ትምህርቱን በተከታተለበት ሀገር የሙያ ስራ ፈቃድ ይዞ ሲያገለግል ከነበረ ኢትዮጵያ ውስጥ ልምምድ ማድረግ ሳያስፈልገው ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎችን ካሟላ የሙያ ፈቃድ ይሰጠዋል
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው የኢንተርንሺፕ ቆይታ ጊዜው በሰንጠረዥ 2 በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡-

**15. Assignment of Foreign-Trained Health Professionals through Internships or Externship Practices**

1. Starting from the basic health care training, any health professional who has received training abroad and applied for health professional registrationand license,shall not be required to conduct aninternship if he/she Submits a license stating thatis registered and was practicing his profession in the country.
2. From the beginning of the training, anyone who has received training abroad and applied for professional registration and license will be assigned for an internship that will not last for six months to one year if he or she is not registere d in the country where he or she is train ed.
3. Subject to the provisions of paragraph (2) of this Article, if the profession is one of the targets of licensure examination nationally, a professional may obtain a professional license after passing a competency assessment exam and fulfilling other requirements.
4. Without prejudice to the provisions of this Article (1) and (2) of this Article, if the professiona l who attended the coure had a prof essional work license and work experience, he would be given a license if he met other conditions without the need to practice in Ethiopia.
5. Sub article 1 of this article internship period shall be as indicated under table 2.

ሰንጠረዥ2. በውጪ አገር ሰልጥነው ለሙያ ምዝገባ የሚቀርቡ ባለሙያዎች ኢንተርንሽፕ (በኤክስተርንሺፕ) ልምምድ የሚቆዩበትን ጊዜ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ተ.ቁ | የሙያዓይነት | የቆይታጊዜ |
|---|---|---|
| 1. | ጠቅላላ ሀኪም | አንድ ዓመት |
| 2. | ስፔሻሊስት ሀኪም | ስድስትወር |
| 3. | ከሀኪም ውጭ የሆኑ ሌሎች ክሊኒካል የሙያ ዘርፎች | ስድስትወር |

6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ ቢኖርም ከውጪ ሀገር ለአጭር ጊዜ ለሚቆይ ስራ፣ ለአደጋ ጊዜ የሰብአዊ እርዳታ ወይም በሚስቴሩ በሚወሰኑ ለሌሎች ጤናአገልግሎቶች ለሚመጣ ባለሙያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ(6) እና (7) ወይም አንቀጽ (6) እና (8) የተጠቀሱትን መስፈርቶች እስካሟላ ድረስ ልምምድ ሳያስፈልግ የሙያ ስራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
7. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ባለሙያውን በጊዚያዊነት ያስመጣው ተቋም
   ሀ) ባለሙያው ተልዕኮውን ሲያጠናቅቅ ወዲያወኑ ለሚስቴሩ የማሳወቅና ፈቃዱ እንዲመልስ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡
   ለ) ባለሙያው በሚሰጠው የጤና አገልግሎት ለሚያደርሰው የሙያ ስህተትና ጉዳት አግባብ ባላቸው ሕጐች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**Table 2: Table which indicates the duration of professionals trained abroad assigned under externship**

| No. | Type of profession | Duration |
|---|---|---|
| 1 | General practitioner | One year |
| 2 | Specialist | Six Months |
| 3 | Other clinical professional departments apart from Medicine | Six Months |

6. Notwithstanding the provisions of the sub-article (5) of this Article, a professional who comes for short-term work, emergency humanitarian assistance or other health services determined by the Ministry shall, in accordance with the provisions of Articles (6) and (7) or Articles (6) and (8) of this Directive As long as you meet the requirements, you can be granted a work permit without training.
7. Subject to sub-article (6) of this Article, the institution that temporarily brought in a health professional
   A) Shall be responsible for informing tothe Ministry as soon as the professional completes its mission and return back the license.
   B) The professional shall be held liable for any misconduct or damage caused by the health service provided by the relevant legislation.

## 16. ምትክ የሞያ ስራፈቃድስለመስጠት

1. ማንኛውም የሙያ ስራ ፈቃዱ የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ወይም የተቃጠለበት ሰው ምትክ የሙያ ስራ ፈቃድ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ምትክ የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡፡
   - ሀ) የሙያ ስራ ፈቃዱ የተበላሸ ከሆነ የተበላሸውን መመለስ፤
   - ለ) የሙያ ስራ ፈቃዱ የጠፋ ወይም የተቃጠለ ከሆነ የጠፋ ወይም የተቃጠለ መሆኑን ከፍትህ አካል ማረጋገጫ ማምጣት፤
   - ሐ) ስድስት ወር ያላለፈው ሁለት የፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍ፤ እና
   - መ) የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ፡፡
3. ሚኒስቴሩ ወይም ክልል ተቆጣሪ አካላት የሙያ ፈቃድ ስለመጥፋቱ እና አስፈላጊው ጥንቃቄ እንዲደረግ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሰርኩላር ደብዳቤ ወይም በጋዜጣ የማሳወቅና የማሳሰብ እንዲሁም ለባለሙያው ምትክ የሙያ ስራ ፈቃድ የመስጠት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

## 16. Granting replacement professional license

1. Any person whose profession al license has been damaged, lost, or burned may apply for a replacement professional license.
2. Any person in order to get a replacement professional license should fulfill the following conditions
   - A) If the professional work license is damaged Should return
   - B) If the professional work license is lost or fired should bring a confirmation from justice entities
   - C) Bring two passport size photographs not more than 6 months and
   - D) Receipt of service renewal payment settlement

3. The Ministry or Regional regulatory bodies shall be responsible for notifying the concerned parties of the loss of professional license ina circular letter or newspaper and for issuing a professional license on behalf of the professional.

## 17. የተሰጠየሞያ ስራፈቃድሚጋጋጥን በተመለከተ፣

በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ተቆጣጣሪ አካላት የስራ ሙያ ፈቃድ የተሰጠው አንድ ባለሙያ ከኢትዮጵያ ውጪ ያለ ሌላ ተቆጣጣሪ ወይም ቀጣሪ አካል የሙያ ስራ ፈቃዱ እንዲረጋገጥለት (verification) ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ቆይታው ስለነበረው ሁኔታ ጉድስታንዲግ ሌተር (Good standing letter) ሊጠየቅይችላል፡፡ በዚህ ጊዜም፡-

1. የሙያ ፈቃዱን የሰጠው አካል የተጠየቀውን የማረጋገጥ (verification) ወይም ጉድስታንዲግ ሌተር (Good standing letter) ይሠጣል፤
2. በዚህ አንቀፅ ተራ ቁጥር '1' ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠያቂው አካል የክልሎችን ምላሽ ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ ሚኒስቴሩ ከክልሎች ጋር በመነጋርና መረጃውን በመለዋወጥ የማረጋገጥ (verification) ወይም ጉድስታንዲግ ሌተር (Good standing letter) ሊሰጥ ይችላል

## 17. Regarding the verification of a professional license

A professional licensed bythe Ministry or regional regulatory bodies may be consulted by a regulator or employer outside of Ethiopia for the validity thelicense given or may request the status of the professional in his/her stay in Ethiopia by a Good Standing letter. In this case:

1. The issuer of the professional license shall issue the required verification or Good standing letter
2. Subject to the provisions of Article 1 of this Article, if the requesting body refuses to accept the response of the States, the Ministry shall consult with the States and exchange information (verification) or Good Standing letter and can verify the document

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. የሙያ ስራፈቃድአሰጣጥ ስርአትን በተመለከተ

ክልሎች የራሳቸውን የሙያ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ ስርአት ሊዘረጉ ይችላሉ

### 19. አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ

ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሙያ ስራ ፈቃድ የሚያሳግድ ወይም የሚያሰርዝ ወይም በወንጀል የሚያስጠይቅ ጥፋት ፈፅሞ ቢገኝ ሚኒስቴሩ ወይም ክልል ተቆጣሪ አካላት እንደአግባብነቱ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም የወንጀል ክስ እንዲመሰረት ሊያደርግ ይችላል::

### 20. የሙያ ስራፈቃድን የሚያሳግዱ ጥፋቶች

ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ሚኒስቴሩ ወይም ክልል ተቆጣሪ አካላት የሙያ ስራ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፡-

1. ከሁለት ጊዜ በላይ ከሙያ ትግበራው ጋር በተያያዘ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ተገቢውን ማስተካከያ ሳያደርግ ሲቀር እንደአግባቡ ከሶስት ወር ላልበለጠ ጊዜ፤
2. ባለሙያው በሙያው ለማገልገል ብቃት የጎደለው መሆኑ አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥና ሲወሰን፤ ውሳኔው የእገዳ ጊዜውን የሚያካትት ይሆናል
3. ባለሙያው በአዕምሮ ህመም ምክንያት ሙያውን በሚገባ መወጣት ካልቻለ የጤና ሁኔታው እስከሚሻሻልና በሀኪም እስኪረጋገጥ፤

## Part Three
## Special Provisions

### 18. Professional Licensing System

States may establish their own professional licensing system.

### 19. Administrative Action

If any health professional commits an offense that entails suspension, revocation, or has committed a criminal act,the Ministry or the regionalregulatory bodies shall take appropriateadministrative action or prosecute him/her.

### 20. Misconduct resulting in Prohibitions

If a health professional is foundguilty of any of the following reasons, the Ministry or the regional state regulatory body may suspend the professional license.

1. More than twice a written warning in connection with the professional practice and found without proper corrections for not more than three months period accordingly.
2. If the professional is found incompetent to practice his profession by an appropriate entity and the decision includesthe subject to the suspension period.
3. If the professional is not able to perfo-rm the profession due to mental illness until the condition improvesandis confirmed by a doctor.

4. ሆን ብሎ የሙያውን ስነ-ምግባር በሚቃረን ሁኔታ ከተሰጠው የሙያ ስራ ወሰን ወይም የጤና ተቋም ደረጃ በላይ ሲሰራ የተገኘ እንደሆነ እንደ አግባቡ ከአንድ ዓመት ላላነሰ ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ፤
5. በተሰጠው የሙያ ስራ ፈቃድ መነሻ በኃላፊነቱ በከፈተው የጤና ተቋም ውስጥ ያልተመዘገበ ወይም የሙያ ስራ ፈቃዱ የታገደበትን ወይም የተሰረዘበትን ወይም የሙያ ስራ ፈቃድ ጨርሶ የሌለውን የጤና ባለሙያ ሲያሰራ የተገኘ እንደሆነ እንደአግባቡ ከሶስት ወር ላላነሰ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ፤
6. ለህብረተሰብ ጤና በሚያሰጋ ሁኔታ የሙያ ብቃት ችግር ወይም የሙያ ስነምግባር ግድፈት ምክንያት ክስ በሚቀርብበት ጊዜ ሚኒስቴሩ ወይም ክልል ተቆጣሪ አካላት ቀርቦ ውሳኔ እስከሚያገኝ፤
7. ባለሙያው በሙያስነ-ምግባር ግድፈት ምክንያት አግባብ ባለው አካል እንዲታገድ ሲወሰን፤ውሳኔው የእገዳ ጊዜውን የሚያካትት ይሆናል
8. ለስረዛ የሚያበቁ ግድፈቶች ሲፈጠሩ ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ወይም ሚኒስቴሩ ወይም ክልል ተቆጣሪ አካላት ቀርቦ ውሳኔ እስከሚያገኝ፤
9. ከጤና ባለሙያነቱ በታገደበት ወቅት ህገ-ወጥ ጥቅም ለማገኘት ሲል የእገዳ ውሳኔውን ጥሶ የጤና ባለሙያነት አገልግሎት ሲሰጥ የተገኘ እንደሆነ ለተጨማሪ አንድዓመት፤ሊታገድ ይችላል፡፡

4. If he/she is found to have intentionally violated the professional ethics and found practicing beyond his/her job description or beyond the the level of the institution for a period of not less than one year and not more than two years
5. Under health institution opened using his/her professional license, if found practicing unregistered professional or whose work permit has been suspended or revoked or terminated by a health professional which has never hadthat professional license. For a period of not less than three months and not more than six months.
6. To the level of serious public health problem, due to professional incompetency or professional misconduct when there is a claimhis/her license will be suspended until get decision by the Ministry or regional regulatory bodies.
7. Due to malpractice, when the decision is made to suspend by an appropriate entity, the decision shall include a period of suspension.
8. In the event of a breach that may lead to professional license cancellation, tillthe matter shall be referred to a court or the Ministry, or a regional body and get decision.
9. If a professional fonud practicing his/her profession using a suspended professional license to get illegal benefit, his/herrofessional license willy be suspended for an additional one year

## 21. የሙያ ስራ ፈቃድን ለመሰረዝ የሚያበቁ ጥፋቶች

ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ሚኒስቴሩ ወይም ክልል ተቆጣጣሪ አካል የሙያ ስራ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል፡-

1. የሙያ ስራ ፈቃዱ የተገኘው ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ፤
2. የጤና ሙያ እውቀቱንና ክህሎቱን ተጠቅሞ ከባድ የወንጀል ድርጊት በመፈጸሙ ተከሶ ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፤
3. በአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 9 የተጠቀሰውን የእገዳ ቅጣት ተላልፎ የጤና አገልግሎት ሲሰጥ የተገኘ እንደሆነ፤
4. ባለሙያው በሙያ ስነ-ምግባር ግድፈት ምክንያት አግባብ ባለው አካል የሙያ ስራ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ሲወሰን፡፡

## 22. የሙያ ስራ ፈቃድ ስለመመለስ

የሙያ ስራ ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ወይም በራሱ ፈቃድ ሙያውን የተወ ወይም የመጣበትን ተልእኮ ያጠናቀቀ ማንኛውም ባለሙያ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ፈቃዱን የመመለስ ስግዴታ አለበት፡፡

## 23. የመተባበር ግዴታ

ይህን መመሪያ ለማስፈፀም እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማንኛውም የጤና ባለሙያዎች እና ጤና ተቋማት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 21. Miss conducts which may result in the cancelationof professional work license

Any health professional if found to be violating the following sub-articles its professional work license may be canceled by the minister or regional state regulatory authority

1. If confirmed to be the professional license is given in providing false educational evidence
2. If comit a heavy crime using his/her professional skill and knowledge and found to be guilty by court.
3. If he is found practicing his/her profession violating the sanction imposed under Article 20, sub-article9
4. If the appropriate entity decides that the professional license shall be canceled due to violation of professional ethics

## 22. Restitution of Professional Licensing

Any professional whose license has been suspended or revoked or who voluntarily relinquishes his or her profession is obliged to return his or her license within ten working days.

## 23. Obligation to cooperate

Any health professional and health institutions who is concerned should cooperate in order to execute this directive.

## 24. ተፈፃሚነትየማይኖራቸውመመሪያዎች

1. የጤና ባለሙያዎች የምዝገባና የሙያ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ አስተዳደርና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 20/2006 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡በተጨማሪም ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ሰርኩላር ደብዳቤ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡
2. በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር ትምህርታቸውን በከታተል ላይ ያሉ የመጨረሻ አመት የጤና ተማሪ (ሮቴቲንግ ኢንተርን) በተቆጣጣሪ አካል መመዝገብ አይጠበቅበትም

## 24. Nonapplicable directives

1. Registration and Professional Licensing Administration and Supervision Directive No. 20/2006 has been repealed by this Directive. In addition, any directive that is inconsistent with this Directivedoes not apply to a circular letter or practice experience in matters covered by this Directive.
2. Final-year students studying at home or abroad are not required to register with regulatory bodies as rotating intern.

## 25. መመሪያውየሚፀናበትጊዜ

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 1/2013 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ዶ/ር ሊያ ታደሰ

ሚኒስትር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጤና ሚኒስቴር

## 25. Effective period of the directive

This directive shall be effective as of March 8/2021.

Dr. Lia Tadesse
Minister
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Health